**HEALTHY BIRTH DAY, INC.**

**(*aka* COUNT THE KICKS)**

**የአጠቃቀም ውሎች**

ከጁላይ 9፣ 2018 ጀምሮ የጸና

**መግቢያ**

የ 501(c)3 ለትርፍ ያልተቋቋመ Healthy Birth Day, Inc. ተልዕኮ Count the Kicks የህዝብ ጤና ግንዛቤ ዘመቻ አማካይነት በማህጸን ሞቶ መወለዶችን ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ነው። Count the Kicks በሶስተኛው አጋማሽ ውስጥ የጽንስ እንቅስቃሴን የመከታተል አስፈላጊነት እና ስልትን ወላጅ ለመሆን እየተዘጋጁ ላሉ ያስተምራል። ነፍሰ ጡር ሴቶች የልጆቻቸውን የእንቅስቃሴዎች ቀጥ በማወቅ እና ለውጥን ካስተዋሉ ለሐኪሞቻቸው ለመንገር ብቃት እንዳላቸው በማሰብ ልጆቻቸውን የማዳን ኃይል አላቸው። የሚከተሉት የአጠቃቀም ውሎች ከ Count the Kicks መተግበሪያችን ጋር የሚኖርዎትን መስተጋብሮች ይገዛሉ።

**የአጠቃቀም ደንቦችን መቀበል**

እነዚህ የአጠቃቀም ደንቦች በእርስዎ እና በኩባንያው፣ ተባባሪዎቹ እና ቅርንጫፎች ("ኩባንያ" ወይም "እኛ") መካከል የተገባ ነው። የሚከተሉት ደንቦች እና ሁኔታዎች፣ በማጣቀሻ (በጋራ፣ እነዚህ "**የአጠቃቀም ውሎች**") በግልፅ ያካተቱ ማንኛውም ሰነዶች የእርስዎን ወደ እኛ Count the Kicks መተግበሪያ (ማለትም የእኛ "**መተግበሪያ**") ተደራሽነት እና አጠቃቀም ጨምሮ ማንኛውም ይዘት፣ ተግባራት እና በ Count the Kicks መተግበሪያ ወይም www.countthekicks.org በሚለው ድረ ገጽ በኩል የሚቀርቡ አገልግሎቶችን ያስተዳድራል።

መተግበሪያውን መጠቀም ከመጀመርዎ በፊት የአጠቃቀም ደንቦቹን ያንብቡ። መተግበሪያውን በመጠቀም ወይም በአጠቃቀም ደንቦቹ ለመስማማት እቀበላለሁ ወይም እስማማለሁ የሚለው አማራጭ ለእርስዎ እንዲገኝ በሚሆን ጊዜ ጠቅ በማድረግ፣ በእነዚህ፣ በዋቢነት እዚህ የተካተቱት፣ [እዚህ ይገኛል] የአጠቃቀም ደንቦች እና የግላዊነት ፖሊሲ ተገዢ ለመሆን ተስማምተዋል። በእነዚህ የአጠቃቀም ደንቦች ለመስማማት ወይም የግላዊነት ፖሊሲውን ለመቀበል የማይፈልጉ ከሆኑ ወደ መተግበሪያው መድረስ ወይም መጠቀም የለብዎትም።

ይህ መተግበሪያ የቀረበው እድሜያቸው 16 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ተጠቃሚዎች ነው። ይህን መተግበሪያ በመጠቀም፣ ከዚህ በፊት ያሉትን ሁሉንም የብቁነት መስፈርቶች ማሟላትዎን ያረጋግጣሉ። ሁሉንም እነዚህን መስፈርቶች የማያሟሉ ከሆነ መተግበሪያው ላይ መድረስ ወይም መጠቀም የለብዎትም።

ለጠቅላላ የውሂብ ጥበቃ መመሪያ ደንቦች ሲባል፣ የውሂብ ተቆጣጣሪ እና የአውሮፓ ህብረት ተወካይ የመገኛ አድራሻው ከታች ይሚገኘው QCI of West Des Moines, Iowa ነው።

በእነዚህ የአጠቃቀም ደንቦች ውስጥ ሁሉ "**የተወሰኑ አገሮች**" የሚለውን በአውሮፓ ህብረት (EU)፣ በአውሮፓ ኢኮኖሚ አካባቢ (EEA) እና በስዊዘርላንድ ውስጥ ያሉ አገሮችን ለማመልከት እንጠቀማለን። በተጠቀሱት አገሮች ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ እንዲያውቋቸው የምንፈልጋቸው ብዙ መብቶች አሉዎት። እነዚህ መብቶች በሚተገበሩባቸው የተወሰኑ አገሮች ውስጥ በማመሳከሪያነት ይገለፃሉ።

**የአጠቃቀም ደንቦቹ ላይ የሚደረጉ ለውጦች**

እነዚህን የአጠቃቀም ደንቦች በኛ ብቸኛ ውሳኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ ልንከልስ እና ወቅታዊ ልናደርግ እንችል ይሆናል። ሁሉም ለውጦች ስንለጥፋቸው ወዲያውኑ በቅጽበት የሚተገበሩ ሲሆን ከዚያ በኋላ በሚኖሩ ሁሉም የድረ-ገጽ መድረሶች እና አጠቃቀም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። በእነዚህ የአጠቃቀም ደንቦች ላይ ለውጦችን ካደረግን፣

ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት ለውጦቹን የመከለስ ዕድል ለማቅረብ በድረ-ገፃችንና በመተግበሪያ ወይም በሌላ መንገድ ማስታወቂያ የምናቀርብ ይሆናል።

የተከለሱ የአጠቃቀም ደንቦችን ከመለጠፍ በኋላ መተግበሪያውን መጠቀም መቀጠልዎ ለውጦቹን እንደተቀበሉ እና እንደተስማሙ ተደርጎ ይወሰዳል። በእርስዎ ላይ የጸኑ ስለሚሆኑ ማንኛውም አይነት ለውጦች መኖራቸውን ለማወቅ ይህንን ገጽ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማየት ይጠበቅብዎታል።

**ግዴታዎች**

እነዚህን የአጠቃቀም ደንቦች በመቀበል ለእኛ የሚሰጡን አንዳንድ ተስፋዎች እዚህ አሉ፡

**የእርስዎ መለያ**

በእኛ መተግበሪያ ላይ መለያ ለመፍጠር ከመረጡ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡

- የይለፍ ቃልዎን በሚስጥር ይይዛሉ።
- እነዚህን የአጠቃቀም ውሎች እና የእኛን የግላዊነት ፖሊሲ እና ህጉን እና ሌሎች ደንቦችን ጨምሮ መለያን ለማንም ሰው አያጋሩም እንዲሁም ደንቦቻችንን ያከብራሉ።
- አላግባብ መጠቀምን ሪፖርት ካላደረጉ ወይም ካልዘጉ በስተቀር በመለያዎ በኩል ለሚከሰቱ ማንኛውም ነገሮች ኃላፊነት አለብዎት።
- በመተግበሪያው ውስጥ የቀረበው መረጃ ለትምህርት ዓላማ ብቻ እና ለምርመራ ወይም ለህክምና እንዳልሆነ እውቅና ይሰጣሉ። የዚህ መረጃ አጠቃቀም ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር በተገናዘበ መልኩ መከናወን አለበት።

**ማሳሰቢያዎች እና መልዕክቶች**

መተግበሪያችንን በመጠቀም በሚከተለው ተስማምተዋል፡

- እርስዎ መተግበሪያችንን ወይም አገልግሎቶቻችን በተመለከተ ማሳወቂያዎችን እና መልዕክቶችን እንድናቀርብልዎ መፍቀድዎን። የእውቅያ መረጃዎ ጊዜ ያለፈበት ከሆነ ጠቃሚ የሆኑ ማስታወቂያዎችን ሊያመልጥዎ እንደሚችል።
- በሚቀጥሉት መንገዶች ማሳወቂያዎችን እና መልእክቶችን ለእርስዎ እንድናቀርብ እንደሚስማሙ፡ (1) በመተግበሪያው ውስጥ ወይም (2) ለእኛ ለሰጡን የዕውቂያ መረጃ በመላክ (ለምሳሌ፡ ኢሜይል፣ የሞባይል ስልክ ቁጥር፣ ቋሚ አድራሻ) የእውቂያ መረጃዎን ወቅታዊ ለማድረግ እንደሚስማሙ።
- Healthy Birth Day, Inc. በማህጸን ሞቶ መወለድን ለመከላከል እና ህፃናትን ለማዳን ባለው ተልዕኮ፣ የእንቅስቃሴ ቆጠራ መረጃዎን ፕሮግራማችንን ለማጎልበት እና ውጤታማነቱን ለማሻሻል አላማ በምርምር፣ ግምገማዎች ወይም ጥናቶች ውስጥ እንድንጠቀም እንደሚስማሙ።

**መብቶች እና ገደቦች**

**እርስዎ የመረጃዎ ባለቤት ነዎት**

ለእኛ የሚሰጡት ሁሉም ይዘቶች፣ ግብረመልስ እና የግል መረጃ ባለቤት ነዎት። መረጃዎን እንዴት እንደምንጠቀምባቸው የሚያደርጓቸውን ምርጫዎች እናከብራለን። እርስዎ እና ኩባንያው ማንኛውም መረጃዎ የግል መረጃን የሚያካትት ከሆነ፣ የግላዊነት ፖሊሲያችን ተገዢ እንደሚሆን ተስማምተዋል።

እርስዎ እና ኩባንያው በግላዊነት ፖሊሲዎቻችን መሰረት እርስዎ ያቀረቡትን ማንኛውም መረጃ እና የግል ውሂብ ላይ ልንደርስ፣ ልናከማች፣ ልንከውን እና ልንጠቀምበት እንደምንችል ተስማምተዋል።

ህጉን ወይንም የማንንም መብት የማይጥስ መረጃን (የአዕምሯዊ ንብረት መብቶችን ጨምሮ) ብቻ ለማቅረብ ተስማምተዋል። እንዲሁም የሚሰጡት መረጃ እውነተኛ እንደሚሆን ተስማምተዋል። ኩባንያው የተወሰኑ መረጃዎችን እንዲያስወግድ በሕግ ሊገደድ ይችላል።

## ሌሎች ይዘቶች፣ ጣቢያዎች እና መተግበሪያዎች

የእኛን መተግበሪያ ወይም አገልግሎቶች በመጠቀም የተሳሳተ፣ ያልተሟላ፣ የዘገየ፣ አሳሳች፣ ሕገ ወጥ፣ ጎጂ ወይም ጎጂ ሊሆን የሚችል ይዘት ወይም መረጃ ሊያጋጥምዎት ይችላል። የእኛን አገልግሎቶች አላግባብ መጠቀምን ሁልጊዜ መከላከል አንችልም እና ለማንኛውም እንዲህ ያሉ አላግባብ መጠቀሞች ተጠያቂ እንደማንሆን ተስማምተዋል።

የሶስተኛ ወገን መተግበሪያዎችን ወይም ከድረ-ገጻችን ወይም ከአገልግሎቶቻችን ጋር ሊገናኙ የሚችሉ የድር ጣቢያዎች ላይ ለመድረስ መፈለግዎን የመወሰን ኃላፊነት አለብዎት። የሶስተኛ ወገን መተግበሪያ ወይም ድር ጣቢያ እርስዎን እንዲያረጋግጥ ከፈቀዱ ይህ መተግበሪያ ወይም ድር ጣቢያ ከእርስዎ ጋር የሚዛመዱ መረጃዎች ላይ ሊደርስ ይችላል። የሶስተኛ ወገን መተግበሪያዎች እና ድር ጣቢያዎች የራሳቸው የህግ ደንቦች እና የግላዊነት ፖሊሲዎች አሏቸው እና እርስዎ መረጃዎን እኛ በማንችለው መንገድ በሚፈልጉት መንገድ እንዲጠቀሙ ለሌሎች ፈቃድ እየሰጡ ሊሆን ይችላል። በተወሰኑ ገደቦች ውስጥ ተፈጻሚነት ባለው ሕግ ብቻ ሊጠየቅ ከሚችለው በስተቀር ኩባንያው ለእነዚህ ሌሎች ድር ጣቢያዎች እና መተግበሪያዎች ኃላፊነት የለውም - እነዚህን በራስዎ ኃላፊነት ይጠቀሙባቸው። እባክዎ የግላዊነት ፖሊሲያችንን ይመልከቱ።

## ገደቦች

ካምፓኒው የእርስዎን የግንኙነቶች ቁጥር ጨምሮ የመተግበሪያችንን ወይም የአገልግሎቶቻችንን አጠቃቀም የመገደብ መብቱ የተጠበቀ ነው። ካምፓኒው እነዚህን የአጠቃቀም ደንቦች፣ የግላዊነት ፖሊሲያችንን ወይም ህግ እየጣሱ ነው ወይም የድር ጣቢያውን ወይም አገልግሎታችንን አለአግባብ እየተጠቀሙበት ነው ብሎ ካመነ ኩባንያው የእርስዎን መለያ የመገደብ፣ የማገድ ወይም የማቋረጥ መብቱ የተጠበቀ ነው።

## የአዕምሯዊ ንብረት መብቶች

ኩባንያው በመተግበሪያችን እና በአገልግሎቶቻችን ውስጥ ያሉት ሁሉም የአዕምሯዊ ንብረት መብቶቹ የተጠበቁ ናቸው። መተግበሪያውን ወይም አገልግሎቶቻችንን መጠቀም በአገልግሎቶቻችን ወይም በመተግበሪያችን ወይም አገልግሎቶቻችን በኩል ያገኙት ይዘት ወይም መረጃ ባለቤትነትን አይሰጥዎትም። ከመተግበሪያው ወይም ከአገልግሎቶቹ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ የዋሉ የንግድ ምልክቶች እና አርማዎች የየባለቤቶቻቸው የንግድ ምልክቶች ናቸው።

## በራስ ሰር መከወን

ለእርስዎ ጠቃሚ የሆኑ ግኑኙነቶችን፣ ይዘት እና ባህሪያት ምክሮችን ለመስጠት የሰጡትን እና ስለእርስዎ ያገኘነውን መረጃ እና ውሂብ እንጠቀማለን። ለምሳሌ፣ ለእርስዎ ምርቶችን እንድንመክር የእርስዎን ውሂብ እና መረጃ ልንጠቀም እንችላለን። መረጃዎን ትክክለኛ እና ወቅታዊ አድርገን ማቆየት እነዚህ ምክሮች ይበልጥ ትክክለኛ እና ተዛማጅ እንዲሆኑ ለማድረግ ያግዘናል።

## የኃላፊነት ማስተባበያ እና ገደብ

## ዋስትና የለም

ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት፣ ኩባንያው እና ተባባሪዎቹ (እና ኩባንያው አገልግሎቶቹን ለማቅረብ አብሯቸው የሚሰሩ) (ሀ) ሁሉንም የተመለከቱ የዋስትና ማረጋገጫዎችን እና ውክልናዎችን (ለምሳሌ፡ የመልካም ንግድ ዋስትናዎች፣ ለአንድ የተወሰነ አላማ ብቁነት፣ የውሂብ ትክክለኛነት እና ጥሰት አልባነት) ያስተባብላሉ (ለ)

አገልግሎቶቹ ያለምንም መቆራረጥ ወይም ስህተቶች እንደሚሰሩ ዋስትና አይሰጥዎትም እና ሐ) አገልግሎቱን (ይዘት እና መረጃን ጨምሮ) በ "አሁን ባለበት" እና "እንደሚገኝ" መሰረት ያቀርባል።

አንዳንድ ህጎች የተወሰኑ ማስተባበያዎችን አይፈቅዱም፣ እናም አንዳንድ ወይም ሁሉም ማስተባበያዎች እርስዎ ላይ ተፈጻሚ ላይሆኑ ይችላሉ።

**ተጠያቂነትን አለማካተት**

በህጉ መሰረት እስከሚፈቀደው ድረስ (ኩባንያው ይህንን ውል የሚቃረን የተለየ የጽሁፍ ስምምነት ካልገባ በስተቀር) ኩባንያው እና ተባባሪዎቹ (እና ኩባንያው አገልግሎቱን ለማቅረብ አብሯቸው የሚሰራ) ለማንኛውም ቀጥተኛ ያልሆነ፣ የአጋጣሚ፣ ልዩ፣ ተከትሎ በመጣ ወይም ቅጣት የሚያስከትሉ ጉዳቶች ወይም ከአገልግሎቶቹ ጋር የተያያዙ የዳታ፣ዕድሎች፣ ዝና፣ ትርፍ ወይም ገቢዎች (ለምሳሌ፡ አስጸያፊ ወይም የስም ማጥፋት መግለጫዎች፣ የአገልግሎት መቋረጥ ወይም ኪሳራ፣ መረጃዎን ወይም ይዘትዎን መጠቀም ወይም መለወጥ) ተጠያቂ አይሆኑም።

በኩባንያው እና በአጋሮቹ (እና አገልግሎቶቹን ለማቅረብ ኩባንያውን አብሯቸው የሚሰራ) በሚከሰሱበት ጊዜ፣ ለሁሉም የይገባኛል ጥያቄዎች ያለባቸው ኃላፊነት፣ ከሚከተሉት ከዝቅተኛው (ሀ)ለአገልግሎት ክፍያ ካወጡት ወርኃዊ ወይም ዓመታዊ ክፍያ አምስት ጊዜ፣ ካለ፣ ወይም (ለ) $1000 ዩኤስ ዶላር (USD) አይበልጥም።

ይህ የተጠያቂነት ገደብ እርስዎ በኩባንያዎ መካከል ያለው ድርድር መሰረት ሲሆን በሁሉም የይገባኛል ጥያቄዎች (ለምሳሌ፡ የዋስትና፣ ጥፋት፣ ቸልተኝነት፣ ኮንትራት፣ ህግ) እና እንዲሁም ኩባንያው ወይም ተባባሪዎቹ እንደዚህ ዓይነት ጉዳት ሊደርስ መቻሉ የተነገራቸው ቢሆን እንኳ እና እነዚህ መፍትሔዎች እንኳን አስፈላጊው ዓላማቸውን ሳይፈጽሙ ቢቀሩ እንኳን ተፈጻሚ ይሆናል።

አንዳንድ ሕጎች የተጠያቂነትን ውስንነት ወይም ገደብ አይፈቅዱም ስለዚህ እነዚህ ገደቦች በእርስዎ ላይ ተፈጻሚ ላይሆኑ ይችላሉ።

**ማቋረጥ**

እርስዎ እና ኩባንያው በእነኚህ የአጠቃቀም ደንቦች ላይ ያላችሁን ስምምነት በማንኛውም ጊዜ አንዳችሁ ለሌላኛው ማስታወሻ በመስጠት ልታቋርጡ ትችላላችሁ። በማቋረጥ ጊዜ፣ አገልግሎቱን የመጠቀም ወይም የማግኘት መብትዎን ያጣሉ። የሚከተሉት ከተቋረጠም ይቀጥላሉ፡

- የእርስዎን ግብረመልስ የመጠቀም እና ይፋ የማድረግ መብቶቻችን፤
- የእነኚህ አጠቃቀም ደንቦች የሚከተሉት ክፍሎች፡ የኃላፊነት ማስተባበያ እና የተጠያቂነት ገደቦች፤ ተቆጣጣሪ ህግ እና የክርክር መፍትሄ እና አጠቃላይ ደንቦች፤
- ከማቋረጡ በፊት ከሁለቱ ወገኖች የሚፈለግ ማንኛውም መጠን እዳ ከተቋረጠ በኋላ እዳ ሆኖ ይቀጥላል።

መለያ ፈጥረው ከሆነ፣ መለያዎን ለመዝጋት ከዚህ በታች ያለውን የግንኙነት መረጃችንን በመጠቀም ሊያነጋግሩን ይችላሉ።

**ተቆጣጣሪ ህግ እና የክርክር መፍትሄ**

በአስቸጋሪ ክስተት ህጋዊ በሆነ ክርክር ውስጥ ከገባን ኩባንያው እና እርስዎ በ Iowa ፍርድ ቤቶች የ Iowa ህግን በመጠቀም ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ፍርድ ቤቶች የዩናይትድ ስቴትስ ህግን በመጠቀም ለመፍታት ተስማምተዋል።

**አጠቃላይ ደንቦች**

በእነዚህ የአጠቃቀም ደንቦች ላይ ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት ማንኛውም ክፍሉ ሊተገበር የማይችል ሆኖ ካገኘው፣ እርስዎ እና እኛ ፍርድ ቤቱ የእርሱን ዓላማ ለማሳካት እንዲቻል ደንቡን ማሻሻል እንዳለበት ተስማምተናል። ፍርድ ቤቱ እንዲህ ማድረግ ካልቻለ እርስዎ እና እኛ የደንቡን ሊተገበር የማይችል አካል እንዲያስወግድ እና ቀሪዎቹን የአጠቃቀም ደንቦች እንዲተገብር ተስማምተናል።

የእነዚህን የአጠቃቀም ደንቦች ጥሰት ለማስከበር የማንሠራ ከሆነ ይህ የእኛን የአጠቃቀም ደንቦች ለማስከበር ያለንን መብት አንስተናል ማለት አይደለም። በእነኝህ የአጠቃቀም ውሎች ስር ያለዎትን መብቶች ያለእኛ ፈቃድ ለሌላ ሰው መስጠት ወይም ማስተላለፍ አይችሉም። ይሁን እንጂ፣ በእነዚህ የአጠቃቀም ደንቦች ስር ያሉንን መብቶች ለኛ አጋሮች ወይም ኩባንያውን ለሚገዛ ድርጅት ያለፈቃድዎ ልንሰጥ እንደምንችል ተስማምተዋል። ለእነዚህ የአጠቃቀም ደንቦች የሶስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች የሉም።

የህግ ማሳሰቢያ ሊሰጠን የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ከታች ባለው "የመገኛ መረጃ" ክፍል ውስጥ አድራሻ ብቻ ነው።

***የመገኛ መረጃ***

እነዚህን የአጠቃቀም ውሎች በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች በሚከተለው አድራሻ መጠየቅ አለባቸው፡

Healthy Birth Day, Inc.
Attn: ዋና ሥራ አስፈፃሚ
PO Box 71093, Clive, IA 50325 USA
1.515.523.5666
info@countthekicks.org

ለጠቅላላ የውሂብ ጥበቃ ደንቦች ዓላማ የተጠቀሱት ሀገራት ነዋሪዎች እነዚህን የአጠቃቀም ደንቦች በተመለከተ ለሚነሱ ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች ሁሉ የአውሮፓ ህብረት ተወካያችንን ሊያነጋግሩ ይችላሉ፡

QCI
Attn: Count the Kicks App Developer
4300 Westown Pkwy Ste 150, West Des Moines, IA 50266
1.515.440.4960
sfinn@qci.com